# “ከወረቀት እስር ወደ ዲጂታል ነጻነት”

**በይበልጣል መኮንን**

እስኪ ለአፍታ ወደ ኋላ መለስ እንበል፡፡ “ያች የጠወለገች የቀበሌ መታወቂያ” በፕላስቲክ ከረጢት (በላሚኔሽን) ታፍና የምትኖረዋን፣ ጫፍና ጫፏ ጠርዝዞ፣ በዓመት ካልታደሰች "አልሰራም" ብላ አላስገባ አላስወጣ የምትለውን የቀበሌ መታወቂያዎን ያስታውሷታል? ፎቶግራፍዎ ላይ ያረፈው ማህተም ተለጥጦ ፊትዎን ሲያበላሸው፣ ወይም በአጋጣሚ ውሃ ሲነካት ቀለሟ ተበላሽቶ ማንነትዎ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ገብቶ ስንት ጊዜ ተናደዋል? ከሁሉም በላይ ደግሞ አንዱ ቀበሌ ያወጣውን ወረቀት ሌላኛው ቀበሌ "አላውቀውም" ሲልዎ የሚሰማዎ ብስጭት የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ አሁን ላይ ይህ ሁሉ ውጣ ውረድ፣ በዘመናዊው ዓለም "የወረቀት ማንነት" ያከተመበት የታሪክ ምዕራፍ እየሆነ መምጣቱን ያመላክተናል፡፡ እነሆ ዛሬ ኢትዮጵያ፣ ይህንን አሰልቺና አድካሚ አሰራር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ልትተካ "ፋይዳ" የተሰኘ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ከፍታለች፡፡

ዓለም እንደ ህንድ እና ኢስቶኒያ ባሉ ሀገራት ፊር ቀዳጅነት በዲጂታል ባቡር እየተምዘገዘገች ነው፡፡ ኢትዮጵያም በዚህ የለውጥ ማዕበል ውስጥ ራሷን አድሳ ተገኝታለች፡፡ "ፋይዳ" አዲሱ የዲጂታል ዘመን “ሙሽራ” ሲባል ብዙዎቻችን በዓይነ ህሊናችን የሚመጣው ሌላ ዓይነት የፕላስቲክ ካርድ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን የዚህ ፕሮጀክት ጥበብ ያለው "ካርድ" መሆን ላይ ሳይሆን "ቁጥር" መሆን ላይ ነው፡፡

"አንድ ሰው አንድ ነው" የሚለው የፋይዳ መርህ፣ እንደ ጣት አሻራ የማይደገም፣ እንደ ዐይን ብሌን የማይመሳሰል ማንነትን ይሰጠናል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1284/2015 ህጋዊ ልደት ያገኘው ይህ ሥርዓት ባዮሜትሪክ (የፊት፣ የጣት እና የዓይን) መረጃዎችን ከስምና አድራሻ ጋር አዋህዶ፣ ባለ 12 አሃዝ የዲጂታል ቁልፍ (FIN) በእጃችን ያስጨብጠናል፡፡ ይህ ቁጥር ዜግነትና ድንበር ሳይገድበው፣ ዕድሜና ፆታ ሳይለይ ለሁሉም ነዋሪ የሚሰጥ የዲጂታል ዓለም ቪዛ ነው፡፡

የፋይዳን ቁጥር በእጅ መያዝ ማለት፣ የመንግሥትና የግል ተቋማትን ደጅ በመጥናት የሚባክነውን ጊዜ እንደመቆጠብ ነው፡፡ አስቡት፣ ባንክ ቤት ሄደው ወረቀት ማገላበጥ ቀርቶ፣ በጣት አሻራዎ ብቻ ማንነትዎ ተረጋግጦ አገልግሎት ሲያገኙ! ዛሬ ላይ ኢትዮ ቴሌኮምን

ጨምሮ ከ30 በላይ ተቋማት ፊታቸውን ወደ ፋይዳ አዙረዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለአዲስ ሂሳብ ከፋቾች፣ የገቢዎች ሚኒስቴር ለግብር ከፋይ መለያ (TIN) ቁጥር አሰጣጥ የፋይዳን ቁጥር እንደ ወርቅ ማስቀመጫ ቁልፍ እየተጠቀሙበት ነው። ይህም ተግባሩ ከቁጥር ባሻገር የአገልግሎት አብዮት አስብሎታል።

መንግሥት እስከ 2018 ዓ.ም ድረስ ከ90 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ወደዚህ ዲጂታል ጣራ ለመሰብሰብ እያደረገ ያለው ሩጫ፣ ኢትዮጵያን ወደ ዲጂታል ኢኮኖሚ የምታደርገውን ጉዞ የሚያሳልጥ ነው።

"መረጃዬ ቢሰረቅስ? ማንነቴ ለሌላ ወገን ቢሰጥስ?" የሚለው ስጋት በሁላችንም ልብ መመላለሱ አይቀርም። የፋይዳ ሥርዓት ግን የደህንነት ጋሻ እና የግላዊነት ክብር በመሆን ለዚህ ስጋት ጠንካራ ምላሽ አለው። ህጉ እንደሚደነግገው የሰጠነው መረጃ የራሳችን ንብረት ነው። ያለ እኛ ግልጽ ፈቃድ ወይም ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መንግሥትም ሆነ ግለሰብ መረጃችንን ሊነካ አይችልም። መረጃው የሚቀመጠው በተራቀቀ የኢንክሪፕሽን (Encryption) ዘዴ ታሽጎ ሲሆን፣ የፕሮግራሙ ሠራተኞች እንኳን ቁልፉን ማግኘት እንዳይችሉ ተደርጎ የተሰራ የቴክኖሎጂ ምሽግ ነው። ይህ እምነትን ከቴክኖሎጂ ጋር ያስተሳሰረ ድልድይ ነው።

እርግጥ ነው፣ ወደ ዲጂታል ዓለም የሚደረገው ጉዞ አልጋ በአልጋ አይደለም። እንደ አገር ሊፈታተኑን የሚችሉ እሾህማ መንገዶች አሉ። አንደኛውና ዋነኛው ፈተና የከተማና የገጠር ልዩነት ነው። ቴክኖሎጂው ከተማ ላይ ፈክቶ፣ ገጠሩ ላይ እንዳይጠወልግ፣ የኢንተርኔትና የመሰረተ ልማት ተደራሽነትን ማስፋት ይጠይቃል።

በሌላ በኩል፣ በሽግግር ወቅት የሚፈጠረው "ሁለት መታወቂያ የመያዝ" ግራ መጋባት እና የሳይበር ጥቃት ስጋትም እንደ ቀላል የሚታዩ አይደሉም። መረጃ ሁሉ በአንድ ቋት ሲሰበሰብ፣ ያንን ቋት መጠበቅ የአገርን ህልውና እንደመጠበቅ ያህል ከባድ ኃላፊነት ነው። እነዚህ ጉዳዮች ከፊታችን ያሉ የቤት ሥራዎች ናቸው።

በአጠቃላይ ፋይዳ ለኢትዮጵያ የቅንጦት ዕቃ ሳይሆን የዘመኑን ባቡር ለመሳፈር የተቆረጠ ቲኬት ነው። ይህ ሥርዓት አስተዳደራዊ ወጪን ቀንሶ፣ የፋይናንስ ተደራሽነትን አሰፍቶ እና የዜጎችን ክብር የሚጠብቅ ቀልጣፋ አገልግሎትን ለማምጣት የተዘረጋ መሰላል ነው።

ነገር ግን፣ የፋይዳ ስኬት የሚለካው በተመዝጋቢዎች ብዛት (በቁጥር) ብቻ ሳይሆን፣ ስርዓቱ ምን ያህል አስተማማኝ፣ ፍትሃዊ እና ሁሉንም ያሳተፈ መሆን ቻለ በሚለው መለኪያ ነው። የመንግሥት ቁርጠኝነት፣ የተቋማት ትብብር እና የዜጎች እምነት ተጣምረው ከሰሩ፣ ያቺ የድሮዋ፣ የተበጣጠሰች የቀበሌ መታወቂያ ታሪክ ሆና፣ በምትኩ አስተማማኝ የዲጂታል ማንነትን ተክለን፣ ኢትዮጵያን ወደ ዲጂታል ብልጽግና ማማ ላይ ለመውጣት "ጊዜው የቴክኖሎጂ፣ ዘመኑ የ"ፋይዳ" ነው!" እላለሁ ሠላም።